ጋር እነዚህ ድርጅቶች አሁን በያዙት የፖለቲካ አካሄዳቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ የዐ
ርቀወሰላም ጥማ ራሱ ላይ ሸብ ሊያደርጉለት ባይሆን አከሌ ቦክ /የጣህ አከሌ/
ሊደፋበት እየጉነጉኑ እንደሆነ መተንበይ የሚያሻው አይደለም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከታጋይ ኀይሎች የሚጠብቀው ግን ይህን አይደለም::—ምሬቱ፣
ብሶት ከአፍ እስከ ገደፉ ደርሶ ፍልቅ ፍልቅ የሚልበት ሕዝብ ከታጋይ ኀይሎች ሊሰማ
በጉጉት የሚጠብቀው፣ ተአንገቢህ ጦርነት አበቃ፣ የጥፋት ዝናም ነተገ፣ በረት የሚ
ደገንብህ የለም ደርቢህን አመነው፣ በሸህ ውጪ፣ በሸህ ውረድ፣ የሚል በሥራት ነው::—
ደረስንልህን እንጂ መጣንብህን አይጠብቅም::— ስመጡበት ሲደርሱበትማ ለሰላም ቷሳ
ደለው ምን ምርጫ አለው? ሙት የሚጠብቅ ማን አለ?

ሀገሬ ቱ፣ "የማን ቤት ጠፍቶ የማ ሊለማ፣ የማ ቤት
ጠፍቶ የማ ሊበጅ፣
ያውሬ መውለጃ ይሆናል እንጂ"

የሚል ቀረርቶ ባንዱ ወገን "የፍየል ወጠጤ..." የሚለው በሌላ ወገን የሚቀራ
ራበት የርኩቻ ምድር እንዳትሆን አሁንም በጽኑ ፊታችንን፣ ጫንቃችንን ወዳከበደው
የጦር መሣሪያችን፣ እሳት ወደጐረሰው ሠራዊታችን ሳይሆን፣ እሳት ወደበላው ሕዝ
ባችን፣ እንጀቱ ወደታሠረው፣ ቆዳው ወደተኮማተረው ወገናችን መለስ አድርገን፣ የተ
ገለ ሥልታችንን፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በርግጥ መቆማችንን ላንዳፍታ ኀሊናችንን አስ
ጨንቀን እንመርምር::—

ድል የሕዝብ ነው!!

ሀቀኛ ትግል ያቸንፋል!!!